**በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን በኖርዌይ የኦስሎ ቅ/ገብርኤልና የአቡነ ተክለሐይማኖት ቤተ ክርስቲያን ህንፃ ቤተ ክርስቲያን አሰሪ ኮሚቲ መተዳደሪያ ደንብ**

**መግቢያ**

ክርስቶስ በደሙ የመሠረታት ሐዋርያት ሰማዕታትና ቅዱሳን አበው በብዙ ተጋድሎና ድካም እስካሁን ያቆይዋትን የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን እምነትና ሥርዓት ቀጣይነት የሚያረጋግጠው በየዘመኑ የሚነሳው ትውልድ እምነቱንና ሥርዓቱን ተረካቢ ሆኖ ሲገኝ ብቻ ነው።

ቤተ ክርስቲያን ስንል ክርስትያኖች ከእግዚአብሄር ጋር የሚገናኙበት የተመረጡት ክርስትያኖች ቤታቸውን ለጾሎት ቤት አድርገው የሚጠቀሙበት ቤት አንደሆነ በሐዋርያት ሥራ ም.፳፬ ቁ.፯ የተገለጸ አና በሐዋርይት ሥራ ም.፳ ቁ.፪፰ መሰርረት ክርስቶስ በደሙ የገዛቸው የክርስቶስ አካሉ የሆነች ቤተክርስቲያን መስራት አና መገልገል አስፈላጊ በመሆኑ ይህንን የተገነዘበችው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን በተለያዩ አህጉራት አብያተ ቤተ ክርስቲያን እያነፀች ተከታዮቿን ስትጥብቅ የቆየችዉ። በዚህም መሰረት በፈቃደ እግዚአብሔር በ1995 እ.አ.አ የተመሰረተው የኦስሎ ቅ/ገብርኤልና የአቡነ ተክለሐይማኖት ቤተ ክርስቲያን ላለፉት 20 አመታት በኪራይ ቤቶች በመጠቀም አቅሙ የፈቀደውን መንፈሳዊ አገልግሎት ለምእመናን እየሰጠ ያለ ሲሆን ፤ነገር ግን የራሱ ቤተክርስቲያን ባለመኖሩ አገልግሎቱን በተፈለገው መጠን ማሳደግ አልተቻለም። **ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ** ምንም መሥራት የማይቻል መሆኑን ህዝበ ክርስቲያኑ አውቆትና ተረድቶት ከከንቱ ውዳሴ ርቆ፣ በአንድ ልቡና፣ በሙሉ ፈቃደኝነት፣ በአስተዋይነት እና በታዛዥነት የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ለመስራት ፈቃደ እግዚአብሔር ይሁን፡፡

በኖርዌይ የኦስሎ ቅ/ገብርኤልና የአቡነ ተክለሐይማኖት ቤተ ክርስቲያን ያለባትን የቦታ ችግር ለመቅረፍ እና የራስዎ የሆነ ህንጻ ቤተክርስቲያን እንዲኖራት የደብሩ ጠቅላላ ጉባኤና የቤተክርስቲያኑ የበላይ ጠባቂ በብጹዕ አባታችን አቡነ ኤሊያስ ገብረእግዚአብሔር የታመነበት ሲሆን ህንጻ ቤተክርስቲያኑን ለመስራትም ሆነ ለመግዛት በሃላፊነት የሚሰራ በቃለ አዋዲዉ ደንብ አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ 18 በሚያዘዉ መሰረት ከምዕመን በጠቅላላ ጉባኤዉ የተመረጠ የህንጻ አሰሪ ኮሚቴ ተቋቁሟል። በኖርዌይ ኦስሎ ቅ/ገብርኤልና የአቡነ ተክለሐይማኖት አጥቢያ ቤተክርስቲያን ሥር የምንኖር ኢትዮጵያውያን በብፁዕ አባታችን አቡነ ኤልያስ ገብረእግዚአብሔር አሳሳቢነትና ጥረት ቤተክርስቲያናችንን በማሳደግና አገልግሎቷን በማስፋት በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን የሚሰባሰቡባት፤ ትምሕርት የሚቀስሙበትና ሃይማኖታቸውን የሚያጠነክሩበት ተቋም እንድትሆን በደብሩ ምዕመናን የተቋቀቋመ ኮሚቴ ነዉ ።ይህም ኮሚቴ የሚሰራዉን ተግባራዊ እንቅስቃሴ ሥርዓት ባለዉ መንገድ ለማካሄድ፣ ግልጽነትና ተጠያቂነት ያለዉ አሰራር እንዲኖር፣የኮሚቴዉን የስራ ድርሻና የሥራ ግንኙነት ለመወሰን እንዲቻል ይህ መተዳደሪያ ደንብ ተዘጋጅቶ ወጥቷል።

**ክፍል ፩**

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ የውስጥ ደንብ በኖርዌይ አስሎ ቅ/ገብርኤልና የአቡነ ተክለሐይማኖት ቤተ ክርስቲያን ህንፃ ቤተክርስቲያን አሰሪ ኮሚቴ መተዳደሪያ ደንብ ቁጥር 1/2006 ዓ.ም ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**፪, ስያሜ**

ይህ ደንብ በህንፃ አሰሪ አና በሰበካው ጉባኤው አስተዳደር ቀርቦ በሊቀ ጳጳሱ ከጸደቀ በኋላ የኦስሎ ቅ/ገብርኤልና የአቡነ ተክለሐይማኖት ቤተክርስቲያን ህንፃ አሰሪ ኮሚቲ መተዳደሪያ ደንብ ተብሎ ይጠራል።

**፫, ትርጓሜ**

**በዚህ መተዳደሪያ ደንብ የተለየ ትርጉም እስካልተሰጠው ድረስ፦**

፩, ቤተ ክርስቲያን ማለት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተወህዶ ቤተክረርስቲያን የአዉሮፓና የምስራቅ አፍሪካ ሊቀ ጳጳስ በሆኑት በብፁዕ አቡነ ኤሊያስ ገብረእግዚአብሔር ሃገረ ስብከት ስር የሚመራው በኖርዌይ አስሎ ቅ/ገብርኤልና የአቡነ ተክለሐይማኖት ቤተ ክርስቲያን ማለት ነው።

፪, ሊቀ ጳጳስ ማለት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን በአውሮፓና በምስራቅ አፍሪካ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳስ ማለት ነው።

፫, ሰበካ ጉባኤ ማለት በኖርዌይ ኦስሎ የቅዱስ ቅ/ገብርኤልና የአቡነ ተክለሐይማኖት ቤተ ክርስቲያን ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባዔ ማለት ነው።

፬, ህንፃ ቤተክርስቲያን አሰሪ ኮሚቲ ማለት በኖርዌይ የኦስሎ ቅ/ገብርኤልና የአቡነ ተክለሐይማኖት ቤተ ክርስቲያንን ለመስራት በጠቅላላ ጉባኤው ስብሰባ የተመረጠና ህንፃ ቤተክርስቲያን አጠቃላይ እንቅስቃሴ የሚያስተባብርና የሚመራ ማለት ነው።

፭, ሊቀ መንበር ማለት ህንፃ ቤት ክርስቲያን አሰሪ ኮሚቲ ሰብሳቢ ማለት ነው።

## ክፍል ፪

### ፬, ህንፃ ቤት ክርስቲያን አሰሪ ኮሚቲ ዓላማና ተግባር

**በኖርዌይ የኦስሎ ቅ/ገብርኤልና የአቡነ ተክለሐይማኖት ህንፃ ቤት ክርስቲያን አሰሪ ኮሚቲ የሚከተሉት ዓላማና ተግባር ይኖረዋል።**

፩. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን እምነትና ሥርዓት ተጠብቆ ክርስቲያኖች በአንድነት የሚጸልዩበት ከእግዚአብሔር ጋር የሚገናኙበት ቤተ ክርስቲያን በማነፅ ኦርቶዶክሳዊነት ከትውልድ ወደ ትውልድ መተላለፍ እንዲችል ለማድረግ፤

፪. በኖርዌይ የኦስሎ ቅ/ገብርኤልና የአቡነ ተክለሐይማኖት ቤተ ክርስቲያን የምትገለገለው የራሱ ቤተ ክርስቲያየን እንዲኖራት ማስቻል

፫.መንፈሳዊ አገልግሎት በተፈለገው መጠን ማሳደግ የሚያስችል በቂና የቤተክርስቲያኒቱን ሥርአት የጠበቀ ቤተ ክርስቲያን ህንፃ የሚሰራበት ወይም የሚገዛበት ሁኔታ ማመቻቸት ።

፬. አባላት አቅም በፈቀደ መጠን ለቤተክርስቲያኒቱ ግንባታ በተለያዩ የምግባረ ሰናይ ሥራዎች ላይ ተሳታፊ እንዲሆኑ ማድረግ፤

፭. ቤተ ክርስቲያኒቱ በምታዘጋጀው ልዩ ልዩ የገንዘብ ማሰባሰብ ዝግጅቶችና አስተዋፅዖች ላይ ምእመኑን እንዲሳተፉ ማድረግ፤

፮.ከሌሎች እህት አቢያተ ክርስቲያናት ጋር ግንኙነት በመፍጥር ለቤተ ክርስቲያን ህንፃ ስራው አስተዋፅዎ እንዲያደርጉ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

፯. ከመንግስታዊና የግል መስሪያ ቤቶች ጋር በመገናኘት ለቤተክርስቲያኒቱ ግዢ ወይም ሥራ፣ እርዳታ የሚገኝበትን ሁኔታዎች ያፈላልጋል፣ ማመቻቸት፤

፰. የህንፃ ቤተክርስቲያን አሰሪ ኮሚቲ አባላት ከሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባዔው ጋር ተቀራርቦ በመስራት ህንፃ ቤተክርስቲያንን የሚገዛበትን ወይም የሚሰራበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

፱. የቤተክርስቲያኑ ግንባታም ሆነ ግዥ አድራሻው በኖርዌይ ኦስሎ ይሆናል.

## ክፍል ፫

### ፭. ህንፃ ቤተክርስቲያን አሰሪ ኮሚቲ የሥራ አመራር መዋቅር

የቤተክርስቲያንዋን ሥራም ሆነ ግዢ የሚከታተልና የሚያስፈጽመዉ የህንፃ ቤተክርስቲያን አሰሪ ኮሚቴ የተለያዩ ንኡስ ኮሚቴዎችንና ኦዲተር ያካተተ መዋቅር ይኖረዋል;;

፩.የህንጻ አሠሪው ኮሚቴ በአሰራር ተጠሪነቱ ለሰበካ ጉባኤው ሲሆን ሕንጻ አሰሪው ኮሚቴ በሚሰራው ሥራ ላይ ሰበካ ጉባኤው ምንም አይነት ጣልቃ ሳይገባበት ያለ ተጽእኖ በነጻነት ይሠራል.

፪. የህንፃ አሰሪው ኮሚቴዉ ከሰበካ ጉባዔው ጋር በአሰራር ለቤተክርስቲያን ግዢ ወይም ሥራ በመመካከርና በመተባበር ይሰራል።

፫, የህንፃ ኮሚቴዉ ለህንፃ ማሰሪያ ወይም ግዢ ብቻ የሚያገለግል የባንክ ሂሳብ ቁጥር ይኖረዋል።

፬,የህንፃ ኮሚቴዉ በወር /2/ ሁለት ጊዜ ስብሰባ ያደርጋል

፭ የህንፃ ኮሚቴዉ የተለያዩ የሥራ ክፍሎች ይኖሩታል።

፮. የቤተ ክርስቲያኗ ኦዲተር ለህንፃ ኮሚቴዉ ኦዲተር ሆኖ ያገለግላል።

፯□ የሰበካ ጉባኤዉ ሊቀመንበር ከኮሚቴው ጋር አብሮ ይሰራል። ይሁን አንጂ በኮሚቴው ስብሰባ ወቅት ቢገኝም ድምፅ መስጠት አይችልም.

፰. የህንፃ አሰሪ ኮሚቴዉ ከግዢ ወይም ከህንፃ ስራ ጋር የተያያዙ አስፈላጊ ሰነዶችን መመርመር ማዘጋጀትና መከታተል ዋና ተግባሩ ሲሆን ምንም አይነት ውልና ክፍያ በራሱ ማድረግ አይችልም። ይሁን እንጂ የቤተክርስቲያንን ግዥ በሚመለከት ኮሚቴው ከሰበካ ጉባኤው ጋር በመሆን በቃለአዋዲው አ. ፲፪(፰) መሰረት ከፍተኛ ውሎችን መዋዋል ባስፈለገ ጊዜ ከሊቀጳጳሱ መመሪያ እየተቀበለ የሚሰራ ይሆናል.

፲. የህንፃ ኮሚቴዉ በየግማሽ አመቱ/6 ወር/ ለጠቅላላ ጉባኤዉ የስራ ክንዉንና የፋይናንስ ሪፖርት ያቀርባል።

፲፩. በሕንጻ አሰሪ ኮሚቴ አና በሰበካ አስተዳደር መካከል አለመግባባት ቢፈጠር ለሊቀ ጳጳሱ ቀርቦ ውሳኔ የምሰጥ ይሆናል .

፲፩. ይህ የህንፃ ቤተክርስቲያን አሰሪ ኮሚቴ የሚከተሉት 7/ሰባት/ የሥራ አመራር ይኖሩታል

ሀ. ሊቀመንበር

ለ. ም/ሊቀመንበር

ሐ . ዋና ፀሐፊ

መ. ገንዘብ ያዥ

ሠ. ሕዝብ ግንኙነት

ረ. ፈንድሬዚንግ ክፍል

ሸ. ፋይናንስ ክፍል

**፯. ሊቀመንበር**

፩. ህንፃ ኮሚቴዉን ይመራል፣ይወክላል፣የህንፃ ኮሚቴዉን ዉሳኔዎች ተግባረዊነቱን ይቆጣጠራል።

፪ . ሊቀመንበሩ የህንፃ ኮሚቴዉን የባንክ ሂሳብ ከሰበካ ጉባኤው ሊቀመንበር ጋር ሆነዉ በሁለቱ በጣምራ ፊርማ ያንቀሳቅሳሉ።

፫. ለህንፃ ስራ የሚዉል ሥራ ማስኪያጃ እስከ 5000-፣/ አምስት ሺ/ ክሮነር ወጭዎችን ያዛል።

፬. ወጪ ደብዲቤዎችንና የተለያዩ ሰነዶችን ይፈርማል።

፭. ከፀሐፊዉ ጋር በመመካከር በፀሐፊዉ በኩል ስብሰባ ይጠራል።

**፯. ም/ ሊቀመንበር**

፩. ሊቀመንበሩ በሌለበት ተክቶ ይሰራል።

፪. ሊቀመንበሩ በሌለ ጊዜ ም/ ሊቀመንበሩ ከሰበካ ጉባኤዉ ሊቀመንበር ጋር ጣምራ ፊርማ የባንኩን ሂሳብ ያንቀሳቅሳል።

፫. ለህንፃ ስራ ወይም ግዥ የሚዉል ገንዘብ ማግኛ ፕሮጀክቶችን ይቀርፃል።

፬. የሥራ ጫና የበዛባቸዉን ክፍሎች ያግዛል፣ ሌሎች ከኮሚቴዉ የሚሰጡትን ተግባሮች ያከናዉናል።

**፰. ዋና ፀሐፊ**

፩. ከሊቀመንበሩ ጋር በመመካከር አጀንዳ ይይዛል፣ስብሰባ ይጠራል፣የስብ ሰባዎችን ቃለ ጉባኤ ይይዛል፣የተያዘዉ ንም ቃ ለጉባኤ በሚቀጥለዉ ስብሰባ ቀን የዉይይት አጀንዳ ከመከፈቱ በፊት ለኮሚቴዉ አቅርቦ ትክክለኛነቱን እንዲረጋገጥ ያደርጋል።

፪. የህንፃ ኮሚቴዉን ፅ/ቤት አስተዳደር በቅልጥፍና እንዲካሄድና መዛግብት በስርአት እንዲያዙ ያደርጋል፣እንዲሁ በቃለጉባኤዉ መሰረት ሥራዎች መሰራታቸዉን ይከታተላል።

፫. በየሥድስት ወር የሚዘጋጀዉን የኮሚቴዉን የሥራ ሪፖርት አቀናጅቶ ያዘጋጃል፣ለኮሚቴዉ ቀርቦ ከፀደቀ በኋላ ሪፖርቱን ለሰበካ ጉባኤዉ፤ ለጠቅላላ ጉባኤዉ እና ለሊቀ ጳጳሱ ያሳዉቃል።

**፱. ገንዘብ ያዥ**

፩. የተጠ ናከረ ለህንፃ መግዣ ወይም መስሪያ የሚዉል የገንዘብ አሰባሰብ ዘዴ እንዲኖር ጥረት ያደርጋል።
፪. የህንፃ ኮሚቴዉን ገንዘብ ሥ ርዓት ባለዉ መ ንገድ ይይዛል፣ ከኖርዌይ ዉጪ ና በኖርዌይ ከተሞች በተለያዩ ኮሚቴዎችና ከተለያዩ ዝግጅቶች የሚሰበሰበዉን ገንዘብ ተከታትሎ ገቢ ያደርጋል።
፫. ከፋይናንስ ሃላፊዉ፣ ከም/ሊቀመንበሩና ከፈንድሬዚንግ ክፍሉ ጋር በመሆን ገቢ ማስገኛዎችን ይቀይሳል፣ ወደ ድርጊት የሚተረጎሙበትን መንገድ ያመቻቻል።

፬. የባንክ ሒሳብ እንቅሳቃሴን ይከታተላል፣ ሰነዶችን በተገቢ መንገድ ይይዛል ፣እንዲሁም የኮሚቴዉን የፋይናንስ እንቅስቃሴ በዓመታዊ የኦዲት ምርመራ እንዲረጋገጥ ሁኔታዎችን ያመቻቻል።

፭. የህንጻ አሰሪ ኮሚቴ የሚጠቀምበትን ደረሰኝ ከሰበካ ጉባኤው በኃላፊነት ተረክቦ ገንዘብ ይሰበስባል

**፲. የሕዝብ ግንኙነት ዘርፍ**

፩. የህንፃ ስራዉን ወይም ግዥዉን አስፈላጊነትና ሂደት በተገቢ መልክ ለምዕመናንና ለማሕበረሰቡ በማሳወቅ ለህንፃ ስራ ወይም ግዢ እንዲነሳሳ ያደርጋል።

፪, የህንፃ አሰሪ ኮሚቴ የሚሰራዉን ስራ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ስራው የደረሰበትን ለምዕመናንና ለህብረተሰቡ መግለጫ የሰጣል።
፫. ምእመናን ገንዘብ እንዲያዋጡና በእወቀታቸዉ እርዳታ እንዲያደርጉ ቅስቀሳና ጉትጎታ ያደርጋል።

፬. ከመንግስትና መንግስታዊ ካልሆኑ መስሪያ ቤቶች ጋር የስራ ግንኙነት በመፍጠር ለህንፃ ስራዉ ወይም ግዢ የሚያስፈልጉት ሰነዶች እንዲቀርቡ ያደርጋል።
፭.የተለያዩ ፖፕሌትና ብሮሽሮችንና በሌሎች የማህበራዊ ድህረ ገፆችን በመጠቀም ምአመናንና ህብረተሰቡን ይቀሰቅሳል

**፲፩. ፈንድሬዚንግ ክፍል**

፩. የተለያዩ ገንዘብ መሰብሰቢያ መንገዶችን ይቀያሳል፣ያፈላልጋል

፪. ለህንፃ ግዢ ወይም ስራ የሚደረጉ ገንዘብ ማሰባሰቢያ ዝግጅቶችን፣ጨረታዎችን፣ሌሎች መንገዶችን በመጠቀም ገንዘብ እንዲሰበሰብ ያደርጋል።

፫.ከገንዘብ ያዡ፣ከምክት ሊቀመንበሩና ከህዝብ ግንኙነት ጋር በመሆን የገቢ ማሰባሰቢያ እቅድ ይነድፋል፤ስራዎቹ በተገቢ መልኩ መፈፀማቸዉን ይከታተላል።

፬. ምዕመናን በማስተባበር የሚያደርጓቸውን የገንዘብ ማሰባሰቢያ ዝግጅቶች በበላይነት ይመራል ያስተባብራል።

**፲፪. ፋይናንስ ክፍል፤**

፩, የፋይናንስ ክፍል ቤተክርስቲያን ለመስራት ወይም ለመግዛት የሚያስፈልገውን የፋይናንስ አቅም ለማሰባሰብና ለማሳደግ ተግቶ ይሰራል።

፪, የፈንድ ሮዚንግ ክፍሉ በሚያደርጋቸዉ የገንዘብ ማሰባሰቢያ ዝግጅቶች ላይ የሚገባውን ገቢ በአግባቡ ተሰብስቦና ተመዝግቦ ወደ ህንፃ አሰሪ ኮሚቴዉ አካውንት መግባቱብ ያረጋግጣል።
፫,. ለህንፃ መግዣ ወይም መስሪያ የሚያስፈልገውን የባንክ ብድር ተከታትሎ ያስፈጽማል።
፬,. ለህንፃ ግዢ ወይም ስራ የሚቀርቡ ጨረታዎችን በማውጣት ሰነዶችን አማርጦ ለውሳኔ ያቀርባል።
፭,. ለህንፃ ግዢ ወይም ስራ የሚደረጉ ክፍያዎች ውሎች በመመርመር በሰዓቱ እንዲከፈሉ ማዘዧ ይሰጣል።
፮. ለሒሳብ ሥራ አስፈሊጊ ሰነዶችን ያዘጋጃል፣ ይይዛል፣ ይቆጣጠራል።

፯ በየወቅቱ የሂሳብ ሪፖርት እያዘጋጀ ለህንፃ ኮሚቴዉ ያሳዉቃል፣ ዓመታዊ ሪፖርት ለጠቅላላ ጉባኤዉ ያቀርባል።

**፲፫,. የህንፃ ቤተክርስቲያን አሰሪ ኮሚቴ የሚከተላቸዉ የአሠራር ስልቶች**

የህንፃ አሰሪ ኮሚቴዉ አባላት በጋራ ተስማምተዉ ዉሳኔ እንዲሰጡ ይጠበቃል፣ካልሆነ ግን በድምፅ ብልጫ ዉሳኔ ይሰጣል።

**፲፬. የህንፃ ቤተክርስቲያን አሰሪ ኮሚቴ ንዑስ ክፍሎች**

ህንፃ ቤተክርስቲያን ለመግዛት ወይም ለመስራት የህንፃ ኮሚቴዉ በስሩ እንዳስፈላጊነቱ የተለያዩ ንዑሳን ክፍሎችን ማቋቋም ይችላል።የንዑሳኑ ክፍሎች አይነትና ብዛት ኮሚቴዉ ወደፊት ይወስናል።

**፲፭ ኦዲተር**

፩. የኮሚቴዉን የስራ ክንዉን እና የፋይናንስ ሪፖርት ትክክል መሆኑን አጣርቶ ለሰበካ ጉባኤዉ፣ ለጠቅላላ ጉባኤና ለሊቀ ጳጳሱ በፅሁፍ ሪፖርት ያቀርባል።

፪, የህንፃ ኮሚቴዉን የሂሳብ መዝገብ አያያዝና አሠራር ደንብን የተከተለና ለብክነት ያልተጋለጠ መሆኑን ይከታተል፣ ይቆጣጠራል፣ጥፋት ተሰርቶ ሲገኝ የእርማት እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል።

## ክፍል ፬

**፲፮. የህንፃ ቤተክርስቲያን አሰሪ ኮሚቴ አባላት መብትና ግዴታ**

**ሀ, መብት**

፩, ህንፃ ቤተክርስቲያን አሰሪ ኮሚቴ አባላት ቋሚ የሆነ የስብሰባ ግዜ ይኖራቸዋል።
፪, የህንፃ ኮሚቴዉ ለሚያስፈልገው የሥራ ማስኬጃ ወጪ እና ለልዩ ልዩ ገንዘብ ማሰባሰቢያ ዝግጅቶች ማከናወኛ የሚውል የገንዘብና የቁሳቁስ ድጋፍ ሲያስፈልገው በኮሚቴዉ የጋራ ዉሳኔ ገንዘብ ወጪ ተደርጎ እንዲሰጥ መጠየቅ ይቻላል። የተፈቀደለትንም በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል።
፫, በየ6/ስድስት/ ወር የስራ እንቅስቃሴና ክንዉን ሪፖርት የማወቅና ለጠቅላላ ጉባኤዉ እንዲቀርብ መጠየቅ መ ብት አለዉ።

**ለ, ግዴታ**

፩, የህንፃ ቤተክርስቲያን አሰሪ ኮሚቴ አባላት በማናቸውም ሁኔታ የሚያገኘውንም ሆነ የሚሰበስበውን ገንዘብ በህንፃ አሰሪዉ ኮሚቴ የባንክ ሂሳብ ቁጥር ገቢ በጊዜዉ መደረጉን የማረጋገጥ ግዴታ አለባቸው።
፪, የህንፃ ቤተክርስቲያን አሰሪ ኮሚቴ አባላት ቤተክርስቲያኒቱን ለምታወጣቸው ሕጎችና ሥርዓትቶች የመታዘዝ ግዴታ አለባቸው።
፫, የህንፃ አሰሪ ኮሚቴ አባላት የተስማሙበትን ስራዎች የመፈፀም ግዴታ አለባቸዉ።
፬, የህንፃ ቤተክርስቲያን አሰሪ አባላት የህንፃ ቤተክርስቲያን ግዢን ወይም ስራን ስኬታማ ለማድረግ መተባበር ይጠበቅባቸዋል።
፭ . የህንፃ ኮሚቴዉን የአሰራር ሚስጥርና ዲስፕሊን የማክበርና ቤተክርስቲያንን ከሚጎዱ ድርጊቶች መታቀብ አለበት።

**፲፯, የህንፃ አሰሪ ኮሚቴ አባላት የአገልግሎት ዘመን**

፩, ህንፃ ቤተክርስቲያን አሰሪ ኮሚቴ የስራ ዘመን የቤተክርስቲያኑ ግዢ ወይም ሥራ እስኪጠናቀቅ ድረስ ነው።
፪, አንድ የህንፃ ኮሚቴ አባል በስራ ምክንያት ወይም በሌላ ምክንያት ከአካባቢው ከተዘዋወረ ወይም ከኮሚቴው ዓላማና ተግባር ውጭ አፍራሽ ስራ ሲሰራ ከተገኘ ከኮሚቴ አባልነቱ ይወገዳል በምትኩም ሌላ አባል አባል በሊቀጳጳሱ አማካኝነት ለጠቅላላ ጉባኤው ቀርቦ በምትኩ ሌላ አባል ይመረጣል።

**፲፰. የህንፃ አሰሪ ኮሚቴዉ የንብረትና የገንዘብ አስተዳደር**

፩, በህንፃ  አሰሪዉ ኮሚቴዉ የሚሰበሰብ ማንኛዉም ገንዘብ በህንፃ አሰሪ ኮሚቴ ለብቻ በተናጠል በተከፈተ የባንክ ሂሳብ  ቁጥር

በቤተክረስቲያኗ ስም ተቀማጭ ይሆናል።

፪, ማንኛዉም በልገሳ ወይም ለህንጻ ቤተክርስቲያን ማሰሪያ ይሁንልኝ ብሎ  ከተሳለ የህንኑ ገንዘብ በህጋዊ የገቢ ደረሰኝ ይስበሰባል በኮሚቴዉ

የባንክ ሂሳብ ተቀማጭ ያደርጋል

፫,የህንፃ  አሰሪዉ ኮሚቴዉ  ንብረቶች በሥርዓት ተመዝግበዉ በፋይናንስ ጉዳይ ሃላፊዉ ሥር ይቀመጣሉ።

**ክፍል ፯**

**፲፱. የደንቡ መሻሻል**

ይህን የህንጻ አሰሪ  ኮሚቴ መተዳደሪያ ደንብ ማሻሻል ቢያስፈልገው በህንጻ አስሪው ኮሚቴ አማካኝነት ለሊቀ ጳጳሱ ቀርቦ  ሊሻሻል ይችላል።

**፳. ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ መተዳደሪያ ደንብ በሊቀጳጳሱ ፊርማ ከጸደቀበት  ከመጋቢት 13. 2006 ዓም  ጀምሮ የጸና ይሆናል።

ብጹአ አቡነ ኤልያስ ገ/አግዚአብሄር

የአዉሮፓና የምስራቅ አፍሪካ ሊቀ ጳጳስ